DeKalb County School District

Digital Dreamers

# ዲጂታል ህልም አላሚዎች የመሣሪያ ተጠቃሚ ስምምነት SY23-24

የ DeKalb ካውንቲ ትምህርት ቤት ዲስትሪክት በትምህርት ዓመቱ (2023-2024 የትምህርት ዘመን) ውስጥ በቅድመ-መዋዕለህጻናት-12ኛክፍሎች ውስጥ ለሚገኙ ተማሪዎች እንዲጠቀሙባቸው አንድ Chromebook ይመድባል፡፡ Chromebooks የ DCSD (የDeKalb ካውንቲ ትምህርት ቤት ዲስትሪክት) ንብረት ሆነው ይቀጥላሉ እና ከዲስትሪክት እና/ወይም ከዓመቱ የመሰብሰቢያ ሂደት ሲወጡ መመለስ አለባቸው።

*መሳሪያው የሚሰጣቸው ተማሪዎች በዚህ ሰነድ ውስጥ የሚገኘውን መመሪያ እንዲሁም ባህሪይ እና የቴክኖሎጂ አጠቃቀምን በተመለከተ የወጡ የት/ቤት፣ መማሪያ ክፍል እና የት/ቤት አውራጃ ፖሊሲ እና አሰራር መከተል አለባቸው፡፡*

*ማነጋገር የሚችሉት ሰው: ጥያቄ ወይም ስጋት ካለዎት እባክዎ የት/ቤትዎን አስተዳዳር ያነጋግሩ፡፡*

## የ Chromebook ስምምነት

*መሳሪያውን መቀበል*

*መሳሪያው ከመሰጠቱ በፊት ወላጆች እና ተማሪዎች ይህን ስምምነት ፈርመው መመለስ አለባቸው፡፡*

*መሳሪያውን መመለስ*

በትምህርት አመቱ መጨረሻ ላይ መሳሪያው ለት/ቤቱ ይመለሳል፡፡ በ DCSD ት/ቤቶች የሚሰጠው መሳሪያ ጥቅም ለሌላ ሰው አይተላለፍም እንዲሁም ተማሪው መሳሪያውን በሰጠው ት/ቤት መማር ሲያቆም ያበቃል፡፡

*በማንኛውም ምክንያት ከት/ቤቱ የተዛወረ፣ ያቋረጠ፣ የተባረረ ወይም የወጣ ተማሪ ባቋረጠበት/በወጣበት ቀን መሳሪያውን መመለስ አለበት፡፡*

*መሣሪያውን መመለስ ያልቻለ ማንኛውም ተማሪ የመሳሪያውን ሙሉ ምትክ ወጪ እና ማናቸውንም መለዋወጫዎች* እስከ $454.23 *ድረስ ለመክፈል ይገደዳል።*

*ብልሽት እና መጥፋት*

*መሳሪያ ለተማሪ በተሰጠበት ወቅት ሆን ተብሎ ወይም በቸልተኝነት ቢበላሽ፣ ቢጠፋ ወይም ቢሰረቅ የተማሪው ወላጅ/አሳዳጊ በዚህ ሰነድ ላይ የተገለጸውን ቅጣት ይከፍላሉ፡፡*

*ቸልተኝነት*

የዲስትሪክቱ አስተዳደር አንድ *መሣሪያ* በተመሳሳዩ የትምህርት ዘመን ውስጥ ብዙ ጊዜ ከተጎዳ እስከ $454.23 ድረስ ያለውን Chromebook ሙሉ መተካትን ጨምሮ የእርምጃውን ሂደት ይወስናል።

*ሀላፊነት ያለበት የመሳሪያ ተጠቃሚ*

በአውራጃው የተሰጡ መሳሪያዎች ሁሉም ተጠቃሚዎች በአውራጃው ፖሊሲ እና በአሰራር *መመሪያዎች IFBGAላይ የተገለጹትን ደንቦች መከተል አለባቸው: ሀላፊነት የተሞላው የ Enterprise Network, JD አጠቃቀም: የተማሪ ስኑ-ስርአት/የተማሪ ስኑ-ምግባር ደንብ እና JS: የተማሪ ቅጣት፣ ክፍያ እና እዳ፡፡* እነዚህን ደንቦች አለመከተል የስነስርአት ቅጣቶችን ያስከትላል፡፡ ሁሉም የዲስትሪክቱ ፖሊሲዎች በ www.dekalbschoolsga.orgይገኛሉ፡፡

*ተማሪ ከት/ቤት ቀጠና ውጪ በሚሆንበት ወቅት ስለመሳሪያው አጠቃቀም የቁጥጥር ሀላፊነት የሚወስደው ወላጅ ነው፡፡ ተማሪዎች መሳሪያውን በመጠቀም በማንኛውም ሰአት እና በየትኛውም ቦታ ተገቢ ያልሆነ ባህሪይ ማሳየት ወይም የተከለከሉ ነገሮችን ማግኘት አይችሉም ፡፡ ት/ቤት ውስጥ ወይም ውጪ ተማሪዎች መሳሪያውን ተገቢ ያልሆነ እንቅስቃሴ ለማድግ ከተጠቀሙበት የስነ-ምግባር ወይም የህግ ቅጣት ይከተላቸዋል፡፡*

*ሚስጥራዊነት*

በዲስትሪክቱ የተሰጠ መሳሪያዎች የ DCSD ንብረት ሆነው ይቆያሉ። እንደዚሁም በመሣሪያው ላይ የሚደረግ ማንኛውም ነገር የግል አይደለም። የአውራጃ ሰራተኛ በማንኛውም ሰአት በአውራጃ የተሰጠውን መሳሪያ ወስዶ ውስጡ ያለውን ይዘት መፈተሽ ይችላል፡፡ Chromebook ከጠፋ ወይም ከተሰረቀ እንዳይሰራ ይደረጋል።

የ DeKalb ካውንቲ ትምህርት ቤት ዲስትሪክት ሁሉንም የህጻናት የኦንላይን የግላዊነት ጥበቃ ህግ (COPPA)፣ የህፃናት የኢንተርኔት ጥበቃ ህግ (CIPA) እና የቤተሰብ ትምህርት መብቶች እና ግላዊነት ህግ (FERPA) እውቅና ይሰጣል።

DeKalb County ት/ቤት አውራጃ የተማሪን የቤት ኔትወርክ፣ መሳሪያ ወይም የኢንተርኔት ግንኙነት አይቆጣጠርም፡፡ ዲስትሪክቱ በዲስትሪክቱ የተሰጠ መሳሪያ አጠቃቀም ይቆጣጠራል፡፡ በተጨማሪም በዲስትሪክቱ የተሰጠ መሳሪያ ከጠፋ ወይም ከተሰረቀ DCSD መገኛ ቦታ ይከታተላል፡፡

አፕሊኬሽን

DeKalb County ት/ቤቶች በሁሉም መሳሪያ ላይ ቀደም-ብለው የሚጫኑ ቁልፍ የሆኑ አፕሊኬሽኖችን አጥንቷል፡፡ ትምህርቱን ለማገዝ አመቱን በሙሉ ተጨማሪ አፕሊኬሽኖች መጫን ይችላሉ፡፡ DeKalb County ት/ቤት ዲስትሪክት ለትግበራዎች መግዣና መጫን ሀላፊነት አለበት፡፡

ፈቃድ ካለው የት/ቤት ሰራተኛ በስተቀር በአውራጃ ከተሰጠው መሳሪያ ላይ አፕሊኬሽን መጫን ወይም ማጥፋት አይቻልም፡፡ "ከእርስ ቤት ማምለጥ" እና መሳሪዎች ውስጥ ያለፈቃድ መግባት አይፈቀድም፡፡

መሳሪያው ቢበላሽ፣ ቢጠፋ ወይም ቢሰረቅ የገንዘብ ቅጣት

ለተማሪው በተሰጠበት ጊዜ መሣሪያው እና/ወይም መገልገያዎቹ ከጠፉ ወይም ከተሰረቁ፣ ሆን ተብሎም ይሁን በቸልተኝነት ተማሪው እና ወላጅ/አሳዳጊ የሚከተሉትን ክፍያዎች የመክፈል ኃላፊነት አለባቸው፡

Chromebook/ ለ Chromebook መሣሪያዎች መለዋወጫ ምትክ

| | |
|---|---|
| የጠፋ/የተሰረቀ/ከጥገናው በላይ የተጎዳ | • $454.23 |
| የተጎዳ - መጠገን የሚችል | • ጉዳት የደረሰባቸው መሳሪያዎች በቤት ውስጥ ጥገና እንደሚሰሩ ለማወቅ በ DCSD ቡድን ይገመገማሉ። ከመጠገን በላይ ከተበላሸ ሙሉ ምትክ ክፍያ ያስፈልጋል። ከላይ ይመልከቱ፡፡ |
| መገልገያዎች/ተቀጥያዎች ብቻ | • Acer Spin511, 311 & 712 የኃይል አስማሚ $41.00<br>• Acer Chrome Tab 10 የቻርጀር ገመድ $41.00<br>• Chromebook Gum Drop መያዣ $15.42 |

**የመሳሪያ ሙሉ መተኪያ ክፍያ የሚያካትተው መሳሪያውን፣ ሁሉንም ተያያዥነት ያላቸው እቃዎች፣ የሶፍትዌር ፈቃድ እና መጫኛን ነው፡፡*

የስርቆት:

*መሳሪያው ለተማሪው በተሰጠበት ወቅት ከተሰረቀ ተማሪው፣ ወላጅ/አሳዳጊ የሚከተሉት ሀላፊነቶች አሉባቸው፡*

- *የትምህርት ቤት አስተዳደርን ማሳወቅ*
- *የፖሊስ ዘገባ ማቅረብ*
- *ሙሉ ምትክ ክፍያ መክፈል*

ከት/ቤቱ በሚዛወሩበት/በሚወጡበት ጊዜ *መሳሪያን ወይም መለዋወጫዎችን መመለስ አለመቻል፡*

*መሣሪያን ወይም ማናቸውንም መለዋወጫዎችን የሚያስተላልፍ ወይም ያወጣ ተማሪ* ለChromebook እና ለ gum drop *መያዣው* እስከ $454.23 (*ሙሉ ምትክ ክፍያ*) የመክፈል ኃላፊነት አለበት።

<u>*የወላጅ ፈቃድ መስጫ እና ነጻ ማድጊያ*</u>

ከስር በመፈረም በዚህ ሰነድ ውስጥ የሚገኙትን *መመሪያዎች ማንበብዎትን እና መረዳትዎን እንዲሁም ለተማሪዎች መሳሪያ መሰጠቱን መቀበልዎትን ያረጋግጣሉ፡፡* Chromebooks የ DCSD ንብረት እንደሆነ እንዲሁም ከዲስትሪክቱ ከወጡ እና/ወይም የዓመቱ መጨረሻ መሰብሰቢያ ሂደት ሲጠናቀቅ መመለስ እንዳለበት ይገነዘባሉ። *ተማሪው መሳሪያውን በሚይዝበት ወቅት መሳሪያው እና ተያያዥነት ያላቸው እቃዎች ላይ ለሚደርስ መበላሸት፣ መጥፋ ወይም መሰረቅ ሀላፊነት እንደሚወስድ ተረድተዋል እንዲሁም በዚህ ሰነድ ላይ የተገለጸውን የገንዘብ ቅጣት ለመክፈል ተስማምተዋል፡፡*

ከት/ቤት *ቀጠና ውጪ ለተማሪው የመሳሪያ አጠቃቀም እና በማንኛውም ገመድአልባ ኔትወርክ የሚገኝ መረጃ ቁጥጥር ሙሉ-በሙሉ ሀላፊነት እደሚወስዱ ተረድተው ተስማምተዋል፡፡ ተማሪዎች* ት/ቤት *ውስጥ ወይም ውጪ መሳሪያውን ተገቢ ላልሆነ ወይም ለተከለከለ እንቅስቃሴ ከተጠቀሙት የስነ-ምግባር ቅጣት እንደሚከተላቸው ተረድተዋል፡፡*

*ሆን ተብሎ ወይም በቸልተኝነት መሳሪያውን በአግባቡ ባለመጠቀም፣ በመጉዳት፣ በመነካካት፣ በመቁረጥ ወይም በማበላሸት ለሚደርስ ብልሽት* DeKalb County *አውራጃው ሀላፊነት እንደማይወስድ እርስዎ እና ተማሪው ተረድተዋል፡፡ ማንኛውም* የ DeKalb ካውንቲ ት/ቤት ዲስትሪክት የበይነመረብ ተቀባይነት አጠቃቀም ስምምነትን የማያሟላ ማንኛውም ተጠቃሚ ተማሪ በአከባቢው የት/ቤት አስተዳደር ቅጣቶች እርምጃዎች ይወሰዳል። *የተማሪ ህግ መጣስ ጥቅሞችን የማግኘት መብትን ከማሳገድ እና ከማቋረጥ ባሻገር ተገቢ የስነ-ምግባር እርምጃ ሊያስከትል ይችላል፡፡*

የወላጅ/አሳዳጊ ስም

(እባክዎ ይጻፉ): ______________________________________________

የወላጅ/አሳዳጊ ፊርማ፡- ______________________________________ ቀን: ____________

# <u>የተማሪ ስምምነት እና ፊርማ</u>

1. ለት/ቤት የተሰጠውን መሳሪያዬን እከባከባለሁ፡፡
    a. ጉዳትን ለመከላከል ሶኬቶች እና አገናኝ ገመዶች መሳሪያው ላይ በጥንቃቄ መሰካት አለባቸው፡፡
    b. መሳሪያዎች በጭራሽ ባልተቆለፈ ሳጥን፣ መኪና ወይም በማንኛውም ቁጥጥር በሌለበት ቦታ መተው የለባቸውም፡፡
    c. ማንኛውም የሶፍትዌር/ሀርድዌር ጉዳዮችን በ Incident IQ – የተማሪ የእርዳታ ዴስክ ፖርታል በኩል ያሳውቁ፡፡
    d. መሳሪያውን በማይጠቀሙበት ወቅት ጥበቃ በሚደረግለት፣ ቁጥጥር የሚደረግበት ሙቀት ባለበት ሁኔታ ውስጥ ያስቀምጡት፡፡
2. ት/ቤት የሰጠኝን መሳሪያ ለሌላ ሰው በፍጹም አላውስም፡፡
3. ምግብ እና መጠጦች ከመሣሪያዬ ራቅ አደርጋለሁ።
4. የእኔንም ሆነ በማንኛውም የት/ቤት ውስጥ የተቀመጠ መሳሪያን አልበታትንም፣ ጄይልብሬክ ወይም ሀክ አላደርግም፡፡
5. በመሳሪያዬ ላይ ምንም አይነት ጥገና ለማድረግ አልሞክርም።
6. ት/ቤቱ የሰጠውን መሳሪያ አብሮት በተሰጠው መያዣ ብቻ በመያዝ ጥንቃቄ አደርግለታለሁ፡፡
7. ት/ቤቱ የሰጠውን መሳሪያ ት/ቤት፣ ቤት ውስጥ ወይም በማንኛውም ቦታ  የምጠቀመው ተገቢ በሆነ እና የት/ቤቱን ደንብ ባከበረ መልኩ ነው፡፡ መሣሪያዬን አግባብ ባልሆነ መንገድ ከተጠቀምኩ በት/ቤቱ የቅጣት እርምጃ ሊወሰድብኝ ይችላል፡፡
8. ትምህርት ቤት በተሰጠው መሳሪያ ላይ ማስዋቢያዎችን (እንደ ተለጣፊዎች፣ ማርከሮች፣ ወዘተ) አላስቀምጥም። ት/ቤት በሰጠው መሳሪያ ላይ የሚገኝ የሲሪያል ቁጥር መለጠፊያን አልጥም/አላበላሽም፡፡
9. በት/ቤት የተሰጠው መሣሪያዬ በማንኛውም ጊዜ ያለማስታወቂያ ለምርመራ እና ቁጥጥር ተጋላጭ እንደሆነ ተገንዝቤያለሁ። <u>መሳሪያው</u> ላይ የምሰራው ወይም መሳሪያውን የማደርገው ነገር ሁሉ ሚስጥር አይደለም፡፡
10. የእኔን የይለፍ ቃል ለመምህር ወይም ከት/ቤት ለመጣ አዋቂ ሰው ወይም ለእኔ ወላጅ/አሳዳጊ ካልሆነ በስተቀር ለሌላ ሰው አልሰጥም፡፡
11. Chromebooks የ DCSD ንብረት እንደሆነ እንዲሁም ከዲስትሪክቱ ሲወጣ እና/ወይም በትምህርት ዓመት መጨረሻ በመሰብሰቢያ ሂደት ወቅት ላይ መመለስ እንዳለበት ተረድቻለሁ።
12. መሣሪያዬን ብጎዳ ወይም ከጠፋብኝ ወይም ከተሰረቀ መሣሪያውን የመተካት ወጪ እንደሚኖርብኝ አውቃለሁ።

በመሳሪያው አጠቃቀም ስምምነት እና በተማሪው ስምምነት ላይ ባሉት ደንቦች እስማማለሁ፡፡

የተማሪ ስም (እባክዎ ይጻፍ): ______________________________

የተማሪ ፊርማ፡- ______________________________ ቀን: ____________